# ከቤት ውጭ እንክብካቤ ለሚሰጣቸው ልጆች እና ወጣቶች መደበኛ የልጅነት እንቅስቃሴዎችን ለመደገፍ የተቀረጸ የተንከባካቢ መመሪያዎች







በጉዲፈቻ እንክብካቤ ውስጥ ያሉ ልጆች እና ወጣቶች በጉዲፈቻ እንክብካቤ ውስጥ ከሌሉ እኩዮቻቸው ጋር ተመሳሳይ የሆነ መደበኛ የልጅነት ልምዶች ማሳለፋቸው አስፈላጊ ነው። የጉዲፈቻ አሳዳጊ ወላጆች፣ ዘመድ ተንከባካቢዎች፣ እና የቡድን እንክብካቤ መስጫ ተቋማት (በዚህ ሰነድ ውስጥ በሙሉ እንደ ተንከባካቢ ተብለው የሚጠሩት) በRCW 74.13.710 የ"ብልህ የወላጅነት" መስፈርት እንዲጠቀሙ ተፈቅዶላቸዋል።

ይህ መስፈርት የአንድ ልጅ ጤናን፣ ደህንነትን እና ጥሩ ፍላጎትን ለመጠበቅ የታቀዱ ጥንቃቄ እና አሳቢ የወላጅ ውሳኔዎች ተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን ይህም የልጁን ስሜታዊ እድገት እና ብልጽግናን ያበረታታል። ለበለጠ መረጃ ወደ **https://app.leg.wa.gov/rcw/default.aspx?cite=74.13.710** ይሂዱ። እንክብካቤ ሰጪዎች በዚህ መስፈርት ላይ በመመርኮዝ በእነሱ እንክብካቤ ውስጥ ያለ ልጅ ወይም ወጣት በመደበኛ የልጅነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፍ ለመፍቀድ የ DCYF ጉዳይ ሠራተኛ ወይም ኤጀንሲ ቅድመ ፈቃድ ሳይኖር ፈቃድ መስጠት ወይም መከልከል ይችላሉ።

"የተለመደ የልጅነት እንቅስቃሴ" ዕድሜን ወይም ለዕድገት ተስማሚ የሆነ "ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሆነ፣ የማበልጸጊያ እና ማህበራዊ የሆነ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል እና ከአሳዳጊው ቀጥተኛ ቁጥጥር ውጭ ለሃያ አራት እስከ ሰባ ሁለት ሰዓታት የሚቆይ የምሽት እንቅስቃሴዎችን ሊያካትት ይችላል። በተገለጹት የጊዜ ገደቦች ውስጥ ቁጥጥርን ጨምሮ የተለመዱ የልጅነት እንቅስቃሴዎች የጀርባ ታሪክ ምርመራ ወይም የቅድሚያ ክፍል ፈቃድ አያስፈልጋቸውም። ፈቃድ ያላቸው አሳዳጊ ወላጆች በWAC 110-148 ውስጥ የሕፃናት ማሳደጊያ ቤቶች ዝቅተኛ የፈቃድ መስፈርቶችን መከተል አለባቸው።

Extended Foster Care (በተራዘመ የጉዲፈቻ እንክብካቤ) ውስጥ ያለ አንድ ወጣት ለጥገኝነት ዓላማዎች "ልጅ" ተብሎ ይቆጠራል እና በWAC 110-90-0170 ውስጥ ያሉትን ኃላፊነቶች ማክበር አለበት፤ አለበለዚያ ወጣቱ የአዋቂ ሰው ሕጋዊ ሁኔታ እና መብቶች አሉት እና ለድርጊቱ ተጠያቂ ነው። ለበለጠ መረጃ ወደ **https://apps.leg.wa.gov/wac/default.aspx?cite=110-90-0170** ይሂዱ።

| የልጅ/ወጣት እንቅስቃሴ ምድብ | የተለመዱ የልጅነት ተግባራት ምሳሌዎችን በተመለከተ ተንከባካቢዎች በተናጥል ማጽደቅ ይችላሉ* | የልጅነት ተግባራት ምሳሌዎችን በተመለከተ DCYF ማጽደቅ* ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማግኘት አለበት። |
|---|---|---|
| *ማንኛውም ድርጊት ከማንኛውም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም ቁጥጥር/የደህንነት እቅድ ጋር በሚጋጭበት ጊዜ የDCYF የጉዳይ ሠራተኛ ማፅደቅ ወይም አዲስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲኖረው ያስፈልጋል። ኤጀንሲው ከልጁ ወይም ከወጣቱ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ወይም ክፍያዎችን እንዲከፍል የሚጠበቅ ከሆነ በቅድሚያ ከDCYF ጉዳይ ሠራተኛ ማጽደቂያ ያስፈልጋል።* | | |
| የቤተሰብ የመዝናኛ ጊዜ | **ልጆች እና ወጣቶች አስፈላጊ እና/ወይም ተገቢውን የደህንነት መሳሪያዎችን እና መከላከያ መሳሪያዎችን ለሁሉም እንቅስቃሴዎች መጠቀም አለባቸው። ለውሃ እንቅስቃሴዎች በቅርበት ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል።**<br>• ፊልሞች<br>• የማህበረሰብ ዝግጅቶች<br>• የቤተሰብ ዝግጅቶች (ከ72 ሰዓታት ያነሰ)<br>• ካምፒንግ (ከ72 ሰዓታት ያነሰ)<br>• ተራራ መውጣት<br>• ጀልባ መቅዘፍ<br>• መዋኘት<br>• ብስክሌት መንዳት<br>• ሌሎች የስፖርት እንቅስቃሴዎች<br>• በወንዞች ላይ መንሳፈፍ<br>• በወንዞች ላይ መጓዝ | ከ72 ሰዓታት በላይ የሆነ ማንኛውም ዝግጅት ወይም እንቅስቃሴ |
| ማህበራዊ/ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ያሉ እንቅስቃሴዎች | ከ72 ሰዓታት **ያነሰ**<br>• ካምፖች<br>• የመስክ ጉዞዎች<br>• ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎች<br>• በእምነት ላይ የተመሰረቱ እንቅስቃሴዎች<br>• የወጣቶች ድርጅት እንቅስቃሴዎች<br>• የስፖርት እንቅስቃሴዎች<br>• የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች<br>• ከእኩዮች ጋር የሚደረጉ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች<br>• ምሽቱን ከአሳዳጊው ቤት ውጪ ማሳለፍ | ከ72 ሰዓታት **በላይ**<br>• ካምፖች<br>• የመስክ ጉዞዎች<br>• ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎች<br>• በእምነት ላይ የተመሰረቱ እንቅስቃሴዎች<br>• የወጣቶች ድርጅት እንቅስቃሴዎች<br>• የስፖርት እንቅስቃሴዎች<br>• የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች<br>• ከእኩዮች ጋር የሚደረጉ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች<br>• ምሽቱን ከአሳዳጊው ቤት ውጪ ማሳለፍ |

**ኤጀንሲው በሚወስደው ወይም በማይወስደው እርምጃ ምክንያት የሚያስከትለው ሆን የተባለ ወይም አላስፈላጊ በደል ካልኖረ በስተቀር ኤጀንሲው ወይም ተንከባካቢው በተሰጠው ሥልጣን ምክንያት ለልጁ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም።*

| የልጅ/ወጣት እንቅስቃሴ ምድብ | የተለመዱ የልጅነት ተግባራት ምሳሌዎችን በተመለከተ ተንከባካቢዎች በተናጥል ማጽደቅ ይችላሉ* | የልጅነት ተግባራት ምሳሌዎችን በተመለከተ DCYF ማጽደቅ* ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማግኘት አለበት። |
|---|---|---|
| *ማንኛውም ድርጊት ከማንኛውም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም ቁጥጥር/የደህንነት እቅድ ጋር በሚጋጭበት ጊዜ የDCYF የጉዳይ ሠራተኛ ማፅደቅ ወይም አዲስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲኖረው ያስፈልጋል። ኤጀንሲው ከልጁ ወይም ከወጣቱ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ወይም ክፍያዎችን እንዲከፍል የሚጠበቅ ከሆነ በቅድሚያ ከDCYF ጉዳይ ሠራተኛ ማጽደቂያ ያስፈልጋል።* | | |
| በሞተር የሚሠሩ መሣሪያዎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች | **ልጆች፣ ወጣቶች እና ተንከባካቢዎች በሞተር የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን እና መሳሪያዎችን በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁሉንም ህጎች ማክበር እና ተገቢውን የመከላከያ/የደህንነት ማርሽ መጠቀም አለባቸው።**<br><br>ከአዋቂዎች ጋር በሞተር የሚሠራ ተሽከርካሪ የሚነዱ **ልጆች እና ወጣቶች** የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም:-<br>• የበረዶ ተሽከርካሪዎች<br>• ለሁሉም ገጸ መሬት የሚሆን ተሽከርካሪ<br>• የዉሃ ላይ ተሽከርካሪ<br>• ትራክተር<br><br>**ቢያንስ** 14 ዓመት የሚሆናቸው ወጣቶች የሚከተሉትን በሞተር የሚንቀሳቀሱ መሳሪያዎችን ወይም ተሽከርካሪን መንዳት ይችላሉ እና በእነዚህ ብቻ አይወሰንም:-<br>• የሳር ማጨጃ ማሽን<br>• የበረዶ ተሽከርካሪዎች<br>• ለሁሉም ገጸ መሬት የሚሆን ተሽከርካሪ<br>• የዉሃ ላይ ተሽከርካሪ<br>• ትራክተር | ዕድሜያቸው ከ14 ዓመት **በታች** የሆኑ ህጻናት እና ወጣቶች በሞተር የሚንቀሳቀሱ መሳሪያዎችን ወይም ተሽከርካሪዎችን (ለምሳሌ የሳር ማሽን፣ ሞተር ሳይክል) እንዲነዱ አይፈቀድላቸውም። |
| መንዳት | • ተንከባካቢው ለመካከለኛ የመንጃ ፍቃድ ሕግ ዓላማዎች እንደ "ወላጅ/አሳዳጊ" ይቆጠራል።<br>• ተንከባካቢው ለልጁ ለመንጃ ፍቃድ ኢንሹራንስ ማቅረብ እና መክፈል እና ህጻኑ 18 አመት እስኪሞላው ድረስ ወይም ሌላ ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ለልጁ የፋይናንስ ተጠያቂነት እስኪሆንለት ድረስ ኢንሹራንስ ለማቅረብ እና ለመክፈል መስማማት አለበት።<br>  – የአሽከርካሪዎች ትምህርት ክፍሎች<br>  – የአሽከርካሪዎች ስልጠና<br>  – የአሽከርካሪዎች ፈተና<br>  – የግል መንጃ ፍቃድ መስጠት | • የDCYF ጉዳይ ሠራተኛ አንድ ወጣት ፈቃዱን ወይም ላይሰንሱን ከማግኘቱ በፊት የWashington ስቴት የትምህርት ፍቃድ ወይም የግል የመንጃ ፍቃድ ጥያቄ (DCYF 02-636) ቅጹን ሞልቶ ለDOL ማቅረብ አለበት።<br>• ወጣቶች የመንጃ ፍቃድ ወይም ፍቃድ ከመጠየቃቸው **በፊት** የመታወቂያ ካርድ (DCYF 11-077-በ DOL ፋይል) ሊኖራቸው ይገባል (ይህ በ-DCYF 02-636 መቅረብ ይቻላል)። |

**ኤጀንሲው በሚወስደው ወይም በማይወስደው እርምጃ ምክንያት የሚያስከትለው ሆን የተባለ ወይም አላስፈላጊ በደል ካልኖረ በስተቀር ኤጀንሲው ወይም ተንከባካቢው በተሰጠው ሥልጣን ምክንያት ለልጁ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም።*

<table>
<tr><th>የልጅ/ወጣት እንቅስቃሴ ምድብ</th><th>የተለመዱ የልጅነት ተግባራት ምሳሌዎችን በተመለከተ ተንከባካቢዎች በተናጥል ማጽደቅ ይችላሉ*</th><th>የልጅነት ተግባራት ምሳሌዎችን በተመለከተ DCYF ማጽደቅ* ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማግኘት አለበት።</th></tr>
<tr><td colspan="3">ማንኛውም ድርጊት ከማንኛውም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም ቁጥጥር/የደህንነት እቅድ ጋር በሚጋጭበት ጊዜ የDCYF የጉዳይ ሠራተኛ ማፅደቅ ወይም አዲስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊኖረው ያስፈልጋል። ኤጀንሲው ከልጁ ወይም ከወጣቱ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ወይም ክፍያዎችን እንዲከፍል የሚጠበቅ ከሆነ በቅድሚያ ከDCYF ጉዳይ ሠራተኛ ማጽደቂያ ያስፈልጋል።</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ጉዞ</td><td>በUnited States (አሜሪካ) ውስጥ ከ72 ሰዓታት በታች የሚቆዩ ሁሉም ጉዞዎች።</td><td>• ከ72 ሰዓታት በላይ የሚቆዩ ሁሉም ጉዞዎች።<br>• ከሀገር ውጪ የሆኑ ሁሉም ጉዞዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">ወደ British Columbia (ብሪቲሽ ኮሎምቢያ፣ BC) ግዛቶች የሚደረጉ ጉዞዎች የBC Rockies፣ Thompson/Okanogan፣ እና Vancouver Coast and Mountains ያሉ እንደ Washington ግዛት 'የድንበር ወሰኖች' ተደርገው ይታሰባሉ እና ከ72 ሰዓታት ያነሰ ጊዜ ከሆነ ከሀገር ውጭ ፈቃድ አያስፈልግም። ከነዚህ ሌላ ያሉ ግዛቶች ከሀገር ውጭ ተደርገው ይታሰባሉ።</td></tr>
<tr><td>ሥራ/ የሕፃናት እንክብካቤ<br>ግብዓት:-<br>www.Lni.wa.gov/workers-rights/youth-employment/prohibited-duties</td><td>ዕድሜያቸው 14 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ወጣቶች እና WAC 296-125ን የሚከተሉ<br>• የሥራ ቃለ መጠይቅ<br>• አሁን ያለውን ሥራ መቀጠል<br>• በትምህርት ቤት ውስጥ ጣልቃ አይገባም<br>ለበለጠ መረጃ ወደ http://apps.leg.wa.gov/WAC/default.aspx?cite=296-125 ይሂዱ</td><td>ልጅነት ማለው ዕድሜያቸው 13 ዓመት ወይም ከዚያ በታች የሆኑ ማለት ነው</td></tr>
<tr><td>የሕፃናት እንክብካቤ<br>የሕፃናት እንክብካቤ መደበኛ ያልሆነ፣ አልፎ አልፎ እና ከ72 ሰዓታት በታች የሆነ እንክብካቤ ነው።</td><td>ዕድሜያቸው 16 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የጉዲፈቻ ወላጆች ሕጋዊ ልጆች የጉዲፈቻ እንክብካቤ የሚያደርጉ ከሆነ ከሦስት ያነሱ ልጆችን ሊከታተሉ ይችላሉ።<br>ፈቃድ ያላቸው ወይም ፈቃድ የሌላቸው የዘመድ እንክብካቤ ውስጥ ያሉ ልጆች ጥንቃቄ የተሞላበት የወላጅነት ደረጃን መሰረት በማድረግ በወጣቶች እና በአዋቂዎች ቁጥጥር ሊደረግላቸው ይችላል።</td><td>በማህበረሰብ ጉዲፈቻ ወላጆች እንክብካቤ የሚደረግላቸው ሕፃናት እና ወጣቶች በሌሎች የጉዲፈቻ ወላጆች እንክብካቤ የሚደረግላቸው ሕፃናትን እና ወጣቶችን መንከባከብ አይችሉም።<br>ወሲባዊ እና አካላዊ ጥቃት የሚፈጽሙ ወጣቶች ልጆችን መንከባከብ አይችሉም።</td></tr>
<tr><td>ሃይማኖታዊ ተሳትፎ</td><td>በልጁ ወይም በወጣቱ ምርጫ ሃይማኖታዊ አገልግሎት ላይ መሳተፍ።</td><td>የልጁ፣ የወጣቱ እና የሕጋዊ ወላጁ ምርጫዎች ሲጋጩ ለጉዳይ ሠራተኛው ያሳውቁ።</td></tr>
</table>

**ኤጀንሲው በሚወስደው ወይም በማይወስደው እርምጃ ምክንያት የሚያስከትለው ሆን የተባለ ወይም አላስፈላጊ በደል ካልኖረ በስተቀር ኤጀንሲው ወይም ተንከባካቢው በተሰጠው ሥልጣን ምክንያት ለልጁ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም።*